የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ ጥር ፴ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No. 20
ADDIS ABABA, 7th February, 2025


**ማውጫ**


ደንብ ቁጥር ፭፻፷፮/፪ሺ፲፯

የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ (ማሻሻያ)………………… ገጽ ፲፯ሺ፮፻፷፩


**Content**


Regulation No. 566/2025

Council of Ministers Investment Incentive (amendment) Regulation…………Page 17661


## ደንብ ቁጥር ፭፻፷፮/፪ሺ፲፯

## የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብን ለማሻሻል የወጣ ደንብ

የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹/፪ሺ፲፪ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፲፯ እና በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፱/፪ሺ፯ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፩፻፳፱ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ፩. አጭር ርእስ

ይህ ደንብ “የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ (ማሻሻያ) ቁጥር ፭፻፷፮ /፪ሺ፲፯” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ማሻሻያ

የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፭፻፲፯/፪ሺ፲፬ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

፩. የደንቡ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ አንቀጽ (፬) ተተክቷል፡-

## REGULATION No. 566/2025

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO AMEND INVESTMENT INCENTIVES REGULATION

**WHEREAS,** it has become necessary to amend the Council of Ministers Investment Incentives Regulation;

**NOW THEREFORE,** this Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 17 of the Investment Proclamation No. 1180/2020 (as amended) and Article 129 Sub Article (6) of the Customs Proclamation No. 859/2014 (as amended).

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the “Council of Ministers Investment Incentive (amendment) Regulation No. 566/2025”.

### 2. Amendment

Council of Ministers Investment Incentives Regulation No. 517/2022 is hereby amended as follows:

1/ Article 4 Sub Article (4) of the Regulations is deleted and replaced by the following new Sub Article (4) :

“ (፬) በውጭ ሀገር በስራ ላይ የሚሰማሩ ሰዎችን ለማሰልጠን ህጋዊ እውቅና ካላቸው የሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ ኢትዮጵያውያን ሰራተኞችን ወደ ውጭ ሀገር በመላክ፡-

ሀ) ከ፪ሺ እስከ ፫ሺ ለሚሆኑ ኢትዮጵያውን የስራ እድል ያስገኘ ለአንድ አመት፤

ለ) ከ፫ሺ፩ እስከ ፭ሺ ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የስራ እድል ያስገኘ ለሁለት አመት፤

ሐ) ከ ፭ሺ በላይ ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያን የስራ እድል ያስገኘ ለሶስት አመት፤ ከንግድ ትርፍ ግብር ነጻ የመሆን ማበረታቻ ተጠቃሚ ይሆናል።”

፪/ የደንቡ አንቀጽ ፲፫ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፫ ተተክቷል፡-

“፲፫. <u>የተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ ነጻ መሆን</u>

፩/ ለኢንቨስትመንት አላማ የሚውሉ ተሽከርካሪዎች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ሆነው የሚገቡበት ሁኔታ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን አይነት እና ባህሪ መሰረት በማድረግ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲገቡ ሊፈቅድ የሚችለው ከፒክ አፕ እና ስቴሽን ዋገን ውጪ ያሉ ተሽከርካሪዎችን ነው።

“ (4) An investor who provides employment opportunities outside of Ethiopia to Ethiopian who have obtained qualification certificate from an institution recognized for providing training to persons who are to be placed in a foreign country shall:

a) be entitled for One year income tax exemption if provides employment opportunity for 2000-3000 Ethiopians;

b) be entitled for Two years income tax exemption if provides employment opportunity for 3001-5000 Ethiopians;

c) be entitled for Three years income tax exemption if provides employment opportunity for more than 5000 Ethiopians. ”

2/ Article 13 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Article 13:

“13. **<u>Exemption of Motor Vehicles from Customs Duties and Taxes</u>**

1/ The total or partial exemptions from customs duties to be granted for motor vehicles used for investment purposes shall be determined by a Directive to be issued by the Ministry based on the type and nature of investment projects.

2/ The exemption from customs duties to be granted by the Ministry in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall not include pickup and station wagon vehicles.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከተው ቢኖርም የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ከመሃል ሀገር ርቀት ባላቸው አካባቢዎች በማእድን፣ በነዳጅ፣ በግብርና፣ በቱሪዝም እና በኮንስትራክሽን ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች የሚጠቀሙባቸውን ፒክ አፕ እና ስቴሽን ዋገን ተሽከርካሪዎችን ከቀረጥ ነጻ እንዲያስገቡ ሊፈቅድ ይችላል፡፡”

3/ Notwithstanding the provisions of Sub Article (1) and (2) of this Article the Ethiopian Investment Board may allow duty free importation of pickup and station wagon vehicles to be used in the remote areas of the country by companies engaged in the mining, petroleum, agriculture, tourism and construction sectors. ”

፫/ የደንቡ አንቀፅ ፲፬ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተሽሮ ከንዑስ አንቀፅ (፪) እስከ (፭) ያሉት ንዑስ አንቀፅ (፩) እስከ (፬) ሆነው ተሸጋሽገዋል።

3/ Sub Article (1) of Article 14 of the Regulation is deleted and Sub Articles (2) to (5) are rearranged as Sub Articles (1) to (4).

፬/ ከደንቡ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀፅ (፫) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፬) ተጨምሯል፡-

4/ The following new Sub Article (4) is added after Sub Article (3) of Article 16:

“(፬) በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ቢኖርም የኢትዮጵያ ኢቨስትመንት ቦርድ ስትራቴጂክ ለሆኑ እና ለእሴት ጭማሪ አጋዥ ለሆኑ የማእድን ወይም የነዳጅ ምርቶችና ስራዎች ተጨማሪ ማበረታቻ ሊፈቅድ ይችላል።”

“ (4) Notwithstanding the provisions of this Article, the Ethiopian Investment Board may grant additional incentives to strategic mining or petroleum operations or products that are needed for value addition.”

፭/ ከደንቡ አንቀጽ ፳፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል፡-

5/ The following new Sub Articles (3) is added after Sub Article (2) of Article 27:

“፫/ ይህ ማሻሻያ ስራ ላይ ከዋለበት ቀን ፊት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባጸደቃቸው የማእድን እና የነዳጅ ስምምነቶች የተፈቀዱ ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ የመሆን መብቶች ተፈጻሚነት ይቀጥላል።”

“3/ Exemptions from customs duties and taxes granted under mining and petroleum agreements signed prior to entry into force of these Regulations with the approval of the Council of Ministers shall remain valid.”

**፫. <u>ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን</u>**

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ጥር ፮ ቀን ፪ሺ፲፯ ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጥር ፴ ቀን ፪ሺ፲፯**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**3. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force from January 14th day 2025 on which it was approved by the Council of Ministers.

**Done at Addis Ababa, this 7th day of February, 2025**

**ABIY AHMED (DR)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**